# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**የከቲተ 12 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**የዓለም ነዳጅ ዋጋ ቀነሰ ወያኔ ግን ሊጨምር ነው፤**

**ዜጎች በርሀብ እንደ ቅጠል እየረገፉ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**ወያኔ የፈራው አልቀረም የህዝብ አመፁ ጅቡቲ ደረሰ፤**

ከቀን ወደ ቀን የኑሮ ውድነቱ እያደገና እየሰፋ ከመርገብ ይልቅ እየተወጠረ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ወያኔ የነዳጅ ዋጋ ሊጨምር መሆኑ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋለጠ፡፡

በአሁኑ ሰዓት የዓለም ነዳጅ ዋጋ 84 የአሜሪካን ዶላር እየተሸጠ ሲሆን የወያኔ ቡድን ግን በ93 ዶላር ዋጋ ተምኖ እየቸበቸበ ከመሆኑም በተጨማሪ ሰሞኑን እንደገና አዲስ የነዳጅ ታሪፍ አወጣሁ በማለት ከፍተኛ ጭማሪ ለማድረግ የሚያስችለውን እቅድ ማውጣቱ ታውቆዋል፡፡

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ከሱዳን የነዳጅ ግዥ እየፈፀመ ያለው የወያኔ ቡድን ከያዝነው የካቲት ወር ጀምሮ ለተከታታይ ሶስት ወራት የነዳጅ ማጣሪያው እድሳት ላይ ስለሚቆይ በሚል የዋጋ ጭማሪ ሊያደርግ መሆኑን የጠቆሙት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በአንድ ሊትር ቤንዚን ላይ ከአንድ ብር በላይ ሊጨምር እንደሚችል እና በህዝቡ ኑሮ ውድነት ላይ ተጨማሪ ሸክም ለመፍጠር እና ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሊከተው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ህዝቡ የዕለት ጉርሱን መሸፈን አቅቶት ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ወድቆ ባለበት ..... ከ5 ሚሊዮን ዜጎች በላይ በርሀብ እየተገረፉ አልፎ ተርፎ በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እንደቅጠል እየረገፉ ባለበት በአሁኑ ሰዓት.... በእሳት ላይ ቤንዚን እንዲሉ ህዝቡ ኑሮ ከብዶት ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ

ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አድርጎ ህዝቡን የከፋ ችግር ውስጥ ሊከተው መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አጋልጠዋል።

ከያዝነው የካቲት ወር ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር መጀመሪያ ድረስ በእድሳት ምክንያት ስራ አቋዋረጠ የተባለው የሱዳኑ የነዳጅ ማጣሪያ ኩባንያ ስራ አስኪያጆች አስቀድመው ለወያኔ ባለስልጣናት እንዲዘጋጁ ከስድስት ወራት በፊት ማስጠንቀቂያ የሰጡ ቢሆንም ወትሮም ለሀገር እና ለህዝብ ደንታ የሌለው ፀረ ህዝብ ቡድን  ችላ በማለት እና የህዝቡን ችግር ወደ ጎን በመተው ሳይዘጋጁ በመቅረታቸው ዛሬ ከፍተኛ የነዳጅ እጥረት ሊከሰት እንደቻለ የጠቆሙት ምንጮቹ ይህንን ተገን በማድረግም የዋጋ ጭማሪ ሊያደርጉ መሆኑ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

ተራ፤ ተልካሻ እና አሳማኝ ያልሆኑ ምክንያቶችን እየደረደረ በህዝብ ላይ የዋጋ ጭማሪ እያደረገ የሚዘርፈው የወያኔ ቡድን የሱዳኑ የነዳጅ ማጣሪያ ኩባንያ ከስድስት ወራት በፊት እንዲያጠራቅምና የአደጋ ግዜ የሚሆን መጠባበቂያ እንዲዘጋጁ ቢያሳስብም ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ከርመው ሲያፌዙና ሲያሾፉ ቆይተው ዛሬ ማጣፊያው ሲያጥራቸው የራሳቸውን ስህተት ህዝቡ እንዲሸከም ከማድረጋቸውም በተጨማሪ በጅቡቲ የወደብ ታሪፍ ጨመረ .....የሱዳን ነዳጅ ማጣሪያ በእድሳት ምክንያት ተዘጋ በሚሉ ሰንካላ ምክንያቶች ከህዝቡ አቅም በላይ ዋጋ ሊጨምሩ መሆኑ ቢታወቅም መቼ እንደሚተገብሩት ምንጮቹ አልገለፁም።

በሀገር ውስጥ አለ የተባለው የነዳጅ ክምችት ከአንድ ወር በላይ እንደማያቆያቸው የገለፁት ምንጮቹ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ለመከላከያ ተብሎ የተቀመጠ መሆኑና በተለይ የህዝቡ መገልገያ የሆነው የምግብ ማብሰያ ላምባ ከዕለት ወደ ዕለት የህዝቡ ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ እጥረቱ በዚሁ ከቀጠለና ከመጠባበቂያው ካለቀ አስቸጋሪ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችልም ምንጮቹ ከወዲሁ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል።

አስገራሚው ነገር ይላሉ ምንጮቹ አስገራሚው ነገር በአሁኑ ሰዓት ነዳጅ በሀገር ውስጥ በቂ ክመችት በሌለበት እና እንደልብ በማያወላዳበት ወቅት እንኩዋን ግዥ ፈፅሞ ለማስገባት ከመሞከር ይልቅ ለመከላከያ እና ለደህንነቱ ተቋዋሞች በቢሊዮን የሚቆጠር ብር መድቦ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ በእጅጉ  የሚሳዝን ነው ብለዋል።

ወያኔ ከስህተቱ ሳይማር ይባስ ብሎ  በስህተት ላይ ስህተት እንደ ድራቶ እየደራረበ ከመሆኑም በላይ ነዳጅ ለአንድ ሀገር ወሳኝ መሆኑን እያወቀ በምን ቸገረኝ ስሜት ህዝቡን በችግር ውስጥ የበለጠ ሊከተው መጣደፉ ከመሆኑም ባሻገር አዲስ ዋጋ ተመን ብሎ ሊቆልልበት መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ይሄንን ሁኔታ በዝመታ ማለፍ ለወያኔ የልብ ልብ መስጠት በመሆኑ ሁሉም በያለበት ሊፋለመው እና አደባባይ ወጥቶ ሊቃወመው ብሎም ሊያወግዘው ግድ ይላል ሲሉም በእልህና በቁጭት ገልፀዋል።

ለመከላከያና ለደህንነቱ መዋቅር በቢሊዮን የሚቆጠር ብር እየመነዘረና እየበተነ ለህዝቡና ለሀገር መሰረታዊ የሆኑትን እቃዎች እና ነዳጅ መደጎም እና ገዝቶ ማቅረብ ያልፈለገው ወያኔ በዋጋ ደረጃም ሆነ በቅርበትም የተሻለ ከሆነው ከሱዳኑ የነዳጅ ኩባንያ ላይ አስቀድሞ ገዝቶ ማጠራቀም ሲገባው በቸልታ

አሳልፎ በሀገሪቱ የነዳጅ ክምችት እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ እና በሚፈጠረው የነዳጅ እጥረት ሳቢያም ህዝቡ ከዚህ የበለጠ የከፋ ችግር ውስጥ እንዲገባ ሆን ብሎ የሰራው መሆኑ ታውቆዋል::

በቅርቡ ይደረጋል ተብሎ በሚጠበቀው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ምክንያት የሸቀጦች እና የእህል ዋጋ ሊንር እንደሚችል ስጋት ያሳደረ ከመሆኑም በላይ በግንባታ ቁሳቁሶች ላይም ከወዲሁ ከፍተኛ ጭማሪ እየታየ መሆኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አረጋግጦዋል::

እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ማስተካከያ ተብሎ አንድ ኩንታል ሲሚንቶ 370 ብር ሲሸጥ የነበረ ሲሆን ሰሞኑን ግን በአንድ ግዜ የ100 ብር ጭማሪ አሳይቶ ከ450 እስከ 470 ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑንና ብረትም ሆነ ሌሎች የግንባታ እቃዎች በፍጥነት ከፍተኛ ጭማሪ እየተደረገባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

በተለይ ለህዝቡ መሰረታዊ ፍጆታ የሆኑት እህልና ጥራጥሬ በትራንስፖርት ታሪፍ መናር ምክንያት ዋጋቸው እያሻቀበ ሲሆን ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ ደግሞ የበለጠ እንደሚጨምር የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ያላቸውን ስጋት እየገለፁ ይገኛሉ::

ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ የወያኔ ቡድን እና የአልበሽር መንግስት በምስጢር ሁሉ አቀፍ ስምምነት የተፈራረሙ ሲሆን ከዚህም መሀከል ወያኔ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እየሰጠ አልበሽር ደግሞ ነዳጅ በግማሽ ዋጋ እየሸጠለት መሆኑን ምንጨቹ አጋልጠዋል::

በሀገር ውስጥ ህዝቡ በመብራት እጦት ማግኘት የሚገባውን ሳያገኝ እየቀረ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ቡድን ለሱዳን ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ሰጥቶ እየቸበቸበ ከመሆኑም በላይ ከካዝና ወጪ ተደርጎ እንደተገዛ በማስመሰል በህዝቡ ላይ ስንጥቅ ትርፍ እያተረፉ መሽጣቸውም ተጋልጦዋል::

በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙት ዜጎች በመብራት ኃይል አቅርቦት እጦት ፋብሪካዎቸ ለሰዓታት....ማሽን ሰራተኞች ለቀናት ...ጋራዥ ሰራተኞች ለሳምንታት በአጠቃላይ ከመብራት ጋር ንክኪ ያላቸው ሰርቶ አዳሪ ዜጎች የእለት ገቢ አጥተው በተቸገሩበት በዚህ ወቅት ለሱዳን ከፍተኛ የመብራት ኃይል ሰጥተው የሀገር ሀብት እና ገንዘብ በጎን በኩል የወያኔ ባለስልጣናት እየዘረፉ እንደሚገኝ ፡ በገሀድ የተጋለጠበት ግዜ ነው ሲሉ ምንጮቹ ጨምረው አጋልጠዋል::

በህዝብ እና በሀገር ላይ ወደር የማይገኝለት ግፍ ለ20 ዓመታት ሲፈፅሙ የኖሩት የወያኔ ባለስልጣናት የህዝቡን ሀብት እየመዘበሩ በተለያዩ ዓለም አቀፍ በንኮች ውስጥ ከማስቀመጣቸውም በላይ እንደ ሌሎች የአፍሪካ መሪዎች ሁሉ በሚስቶቻቸውና ቅምጦቻቸው ሳይቀር ገንዘቡን በወርቅና በሌሎች መሰል ውድ እቃዎች ጭምር እያግበሰበሱ ህዝቡን እና ሀገሪቱዋን እርቃናቸውን እያስቀሩዋቸው መሆኑ በገሀድ እየታየ ያለ ሀቅ መሆኑ ተረጋግጦዋል::

ዛሬ የሰሜን አፍሪከና የመከከለኛ ምስራቅ ሀገራት ህዝቦች በመሪዎቻቸው በሚደርስባቸው ሰብአዊ መብት ጥሰት እና የኢኮኖሚ ድቀት የተነሳ ህዝቡ አመጽ አንስቶ ብዙዎቹን እየሸኘ እና እያባረረ ሲሆን

ከዚሁ የኢኮኖሚ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ሰሞኑንም የጅቡቲ ህዝብ አመፅ መጀመሩ ለወያኔ ከፍተኛ ስጋት ፈጥሮበት እንደሚገኝ ለቤተ መንግስት ቅርበት ያላቸው ወገኖቸ ጥቆማ ያስረዳል፡፡

በሰሜን አፍሪካ ሀገራት በቱኒዚያና በግብፅ ህዝቡ አምባገነን መሪዎቹን ማባረር የጀመረው አመፅ ቀድሞ የኢትዮጵያ ይዞታ በሆነችው በጅቡቲ ውስጥም የሀሰን ጉሌድ ኦብቲዶን አገዛዝ ሰለቸን..... መረረን....አንገሸገሸን .... በማለት በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ጅቡቲያውያኖች በህብረት አደባባይ ወጥተው ተቃውሞ ከማሰማታቸውም በላይ ከታጣቂ ኃይሎች ጋር ግብ ግብ እየፈጠሩ እንደሚገኙ ታውቆዋል፡፡

ከህዝቡ አፍ ላይ እየነጠቀ ከቸርቻሪነት ተለውጦ ዛሬ ኢንቨስተርነት ደረጃ ላይ የደረሰው የጀቡቲው መሪ በሚስቱ እና በልጆቹ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ ጭምር ትላልቅ ህንፃዎችን ከመገንባት አልፎ በባሌ ሰፊ የእርሻ መሬት ተረክቦ ውጭ ሀገር የስንዴ ምርት ኤክስፖርት እያደረገ እና እየቸበቸበ አንቱ ለመባል የበቃ ቱጃር ከመሆኑም አልፎ ከህዝቡ አፍ ላይ እየነጠቀ ለርሀብ እና ለሞት በመዳረጉ ህዝቡ አመፅ ለማንሳት እንደተገደደ የገለፁት ታዛቢዎቸ ይሄ ጉዳይ ለወያኔ መሪዎችም አሳሳቢ በመሆኑ አጣብቂኝ ውስጥ እየገቡ እንደሚገኙ አመላካች ነው ብለዋል፡፡

በአንድ ወቅት አንድ ጥናት እንዳጋለጠው ከሆነ የወያኔ መሪዎች በተለያዩ የዓለም አቀፍ ባንኮች ውስጥ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር አስቀመጠው እንደሚገኙ፤ በተለይ መለስ ዜናዊ ዑጋንዳ ግዙፍ ፋብሪካ አቁዋቁሞ በልጆቹ ስም እየሰራ ከመሆኑም በተጨማሪ ሚስቱ በሁሉም የንግድ ዘርፎች ውስጥ ገብታ እየመዘበረች ከመሆኑም በላይ በኤች አይ ቪ ኤድስ ህመምተኞች ስም በብዙ ሚሊዮን ዶላር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ጥሬ ገንዘብ ያለ አንዳች ሀፍረት እና ይሉኝታ እያግበሰበሰች ወደ ውጭ ባንኮች እያሻገረች መሆኗ ተገልጧል፡፡ በሌላ በኩል በአሁኑዋ ደቂቃ በኢትዮጵያ ዜጎች በርሀብ እየሞቱ ቀባሪ አጥተው የአውሬ ሲሳይ ሆነው የሚገኙበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡

እነዚህና መሰል በደሎች በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ለ20 ዓመታት ሰፈፀም የቆየ ሲሆን አሁን ግን ገደቡን አልፎ የመጣ በመሆኑ እንደ ጎረቤት ሀገር ጅቡቲና እንደ ሌሎቹ የአፍሪካ ህዝቦች በኢትዮጵያም ብጥብጥ እና የህዝብ አመፅ መነሳቱ አይቀሬ ነው በማለት በርከታ ዜጎቸ ያላቸውን ግምት እና ስጋት ሲገልፁ ተደመጠዋል፡፡

በህዝብ እና በሀገር ላይ በፈፀሙት ወንጀል ሌት በህልማቸው ቀን በውናቸው እያባነናቸው የሚቀዡት የወያኔ ባለስልጣናት ከቅርብ ግዜ ወዲህ በሰሜን አፍሪካ የተጀመረው የህዝብ አመጽ ተስፋፍቶ በጎረቤት ሀገራት ሱዳን እና ጅቡቲ መዛመቱ እጅግ ከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ ከትቶዋቸው በመገኘቱ እና እዚህም ሊከሰት ይችላል በሚል ስጋት ተወጥረው በብረት ለበስ የጦር መሳሪያና መትረየስ በጠመዱ ፓትሮሎች እንዲሁም በእግረኛ ወታደሮች እና የፌዴራል ፖሊሶች ጥብቅ ጥበቃ እያደረጉ ቢሆኑም የህዝብ ኃይል ማዕበል በመሆኑ ደርምሶ እንደሚያልፍ ጥርጥር እንደሌላቸው ብዙ የሀገሪቱ ዜጎች በድፍረት በየጎዳናው ላይ ሲገልፁ ይደመጣሉ፡፡

ሰሞኑን በጅቡቲ ውስጥ የተከሰተውን የህዝብ አመፅ ተከትሎ የወያኔ ቡድን በሀገር ውስጥ በከተሞች ከሚያደርጋቸው ጥብቅ ጥበቃ በተጨማሪ  አንድ ብርጌድ ጦር ወደ ድንበር ያስጠጋ ሲሆን ይህም ሻዕቢያ ይህን ግርግር ተጠቅሞ ሊገባ ይችላል አሊያም ከጅቡቲ ሾልከው የሚመጡ አመፅ ቀስቃሾች ሊኖሩ ይችላሉ በሚል ስጋት መሆኑን ከመከላከያ ምንጮች ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል፡፡

በተለይ በትግራይ በአንድ የጦር ሰፈር ውስጥ ለዚሁ የአድማ ብተና እና ለከተማ ችግር ፈቺ ተብሎ ልዩ ኮማንዶ ጦር በምስጢር እየሰለጠነ ሲሆን በቅርቡም ወደ አዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ሊገባ እንደሚችልም የመከላከያ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በህወሀቱ በረሀ አመጣሽ በብ/ጄ/ል መሐመድ ይሻ የሚመራው ይህ የኮማንዶ ጦር በሌሊት እና በቀን ከፍተኛ ልምምድ ከማድረጉም በላይ ችግር ቢፈጠር ያለ አንዳች ርህራሄ እርምጃ እንዲወስድ ሙሉ ስልጣን የተሰጠው ሲሆን አዛዡም  ግንኙነቱ ከመለስ ዜናዊ ጋር ብቻ መሆኑነ ምንጮቹ ጨምረው አጋልጠዋል፡፡